بسم الله الرحمن الرحيم

أسئلة وأجوبة فى العقيدة

ሥ_1) مَنْ رَبُّكَ؟ ጥ _1 :- ጌታህ ማን ነው?

ሙ_1 :- ጌታዬ የላቀው አላህ ነው።: ج_ ١) رَبِّيَ اللهُ تَبَارَكَ وَتَعَالَىٰ

ሥ_2) أَيْنَ اللهُ تَبَارَكَ وَتَعَالَىٰ؟ ጥ _2 :- የላቀው አላህ የት ነው?

ج_ ٢) الرَّحْمٰنُ عَلَىٰ الْعَرْشِ اسْتَوَىٰ.

ሙ_2 :- አርረህማን (አላህ) ከዐርሹ በላይ ከፍ ያለነው።:

ሥ_3) لِمَاذَا خَلَقَنَا اللهُ تَعَالَىٰ؟

ጥ _3 :- የላቀው ጌታችን አላህ ለምን ፈጠረን?

ج_ ٣) لِنَعْبُدَهُ وَحْدَهُ.

ሙ_3 :- እርሱን በብቸኝነት እንድንናመልከው ነው።:

ሥ_٤) مَا حَقُّ اللهِ عَلَىٰ الْعِبَادِ؟

ጥ _4 :- የአላህ መብት በባሮቹ ላይ ምንድን ነው?

ج_ ٤) أَنْ يَعْبُدُوهُ وَلَا يُشْرِكُوْا بِهِ شَيْئًا.

ሙ_4 :- እርሱን በብቸኝነት እንድገዙት በእርሱም ምንንም ፤ማንንም ላያጋሩበት ነው።:

ســ ٥) مَا أَعْظَمُ وَاجِبٍ عَلَيْنَا؟

ጥ _5 :- በእኛ(በሰው ልጆች) ላይ ያለብን ትልቁ ግዴታ ምንድን ነው?

جـ ٥) هُوَ تَوْحِيْدُ اللهِ.

መ_5 :- እርሱም:- አላህን በብቸኝነት ማምለክ ነው::

ســ ٦) مَا هِيَ كَلِمَةُ التَّوْحِيْدِ؟

ጥ _6 :- የተውሂድ ቃል ምንድንናት?

جـ ٦) لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ. መ_6 :- "ላኢላህ ኢልለልኧህ" ናት::

ســ ٧) مَا مَعْنَىٰ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ؟

ጥ _7 :- የ"ላኢላህ ኢልለልኧህ" ትርጉም ምንድን ነው?

جـ ٧) لَا مَعْبُوْدَ بِحَقٍّ إِلَّا اللهُ.

መ_7 :- ከአንድ አላህ በስተቀር በሀቅ (በተገቢነት) የሚመለክ አምላክ የለም ነው::

ســ ٨) مَا أَعْظَمُ الذُّنُوْبِ عِنْدَ اللهِ؟

ጥ _8 :- አላህ ዘንድ ከወንጀሎች ሁሉ ትልቁ (ከባዱ) ወንጀል ምንድን ነው?

جـ ٨) الشِّرْكُ بِاللهِ. መ_8 :- በአላህ ማጋራት ነው::

سـ٩) مَا هُوَ الشِّرْكُ؟

ጥ _9 :- "ሽርክ" (በአላህ ላይ ማጋራት) ምንድን ነው?

جـ ٩) هُوَ عِبَادَةُ غَيْرِ اللهِ، أَوْ عِبَادَةُ غَيْرِهِ مَعَهُ.

መ_9 :- እሱም (ሽርክ) ከአላህ ውጪ ያለን አካል ማምለክ ወይም ከአላህ ጋር ሌላን አካል ማምለክ ነው።።

سـ١٠) مَا دِينُكَ؟ ጥ _10 :- እምነትህ ምንድን ነው?

جـ ١٠) دِيْنِيَ الْإِسْلَامُ. መ_10 :- እምነቴ ኢስልምና ነው።።

سـ١١) مَا مَعْنَىٰ الْإِسْلَامُ؟

ጥ _11 :- "የኢስላም " ትርጉሙ ምንድን ነው?

جـ ١١) هُوَ الْإِسْتِسْلَامُ لِلَّهِ بِالتَّوْحِيْدِ، وَالْإِنْقِيَادُ لَهُ بِالطَّاعَةِ، وَالْبَرَاءَةُ مِنَ الشِّرْكِ وَأَهْلِهِ.

መ_11 :- "ኢስላም ማለት"፡- አላህን በብቸኝነት በማምለክ ላይ ለእርሱ ማንነትን ተገዢ ማድረግ፣ ለትዕዛዛቶቹም መነተት፣ በአላህ ከማጋራት እና ከአጋሪያን መጥራት።።

سـ١٢) كَمْ أَرْكَانُ الْإِسْلَامِ؟

ጥ _12 :- የኢስልምና መሠረቶች ስንት ናቸው?

جـ ١٢) أَرْكَانُ الْإِسْلَامِ خَمْسَةٌ وَهِيَ:- شَهَادَةُ أَن لَّا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ، وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ، وَإِقَامُ الصَّلَاةِ، وَإِيْتَاءُ الزَّكَاةِ، وَصَوْمُ رَمَضَانَ، وَحَجُّ الْبَيْتِ.

መ_12 :- የኢስልምና መሠረቶች አምስት ናቸው እነሱም:-

1ኛ: ከአላህ በስተቀር በሀቅ የሚመለክ አምላክ አለመኖሩንና ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣

2ኛ: ሶላትን በደንቡና በአግባቡ መስገድ፣

3ኛ: ዘካን መስጠት ፣ 4ኛ: የረመዳንን ወር መፆም ፣

5ኛ: የአላህን ቤት መጎብኘት (ሀጅ ማድረግ) ናቸው::

ሠ١٣) كَمْ أَرْكَانُ الْإِيمَانِ؟

ጥ_13 :- የኢማን መሠረቶች ስንት ናቸው?

جـ ١٣) أَرْكَانُ الْإِيمَانِ سِتَّةٌ وَهِيَ:- أَنْ تُؤْمِنَ بِاللهِ، وَمَلَائِكَتِهِ، وَكُتُبِهِ، وَرُسُلِهِ، وَالْيَوْمِ الْآخِرِ، وَبِالْقَدَرِ خَيْرِهِ وَشَرِّهِ كُلِّهِ مِنَ اللهِ تَعَالَىٰ.

መ_13 :- የኢማን መሠረቶች ስድስት ናቸው እነሱም:-

1ኛ: በአላህ ጌትነት ማመን፣ 2ኛ: በመላዓክቶች ማመን፣ 3ኛ: በመፅሓፍቶች ማመን፣
4ኛ: በመልዕክተኞች ማመን፣ 5ኛ: በመጨረሻው ቀን (በትንሳዔ ለት) ማመን፣
6ኛ: በአላህ ውሳኔ በመልካሙም በክፉውም፤ ሁሉም ከላቀው አላህ ዘንድ መሆኑን ማመን ናቸው::

ሠ١٤) مَنْ هُوَ أَوَّلُ رَسُوْلٍ؟

ጥ _14 :- የመጀመሪያው መልዕክተኛ ማንነው?

جـ ١٤) نُوحٌ عَلَيْهِ السَّلَامُ.

መ_14 :- ነቢዩላህ ኑህ(ዐለይሂሰሰላም) ናቸው::

ســ١٥) مَنْ هُوَ آخِرُ الرُّسُلِ؟

ጥ _15 :- የመጨረሻው መልዕክተኛ ማንናቸው?

جـ ١٥) مُحَمَّدٌ صَلَّىٰ اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ.

መ_15 :- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ናቸው::

ســ١٦) مَنْ هُمْ أُوْلُوْا الْعَزْمِ مِنَ الرُّسُلِ؟

ጥ _16 :- የቆራጥነት ባለቤቶች የተሰኙ መልዕክተኞች እነማንናቸው?

جـ ١٦) نُوْحٌ، وَإِبْرَاهِيْمُ، وَمُوْسَىٰ، وَعِيْسَىٰ، وَمُحَمَّدٌ عَلَيْهِمُ الصَّلَاةُ وَالسَّلَامُ.

መ_16 :- ኑህ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ዒሳ እና ሙሐመድ (ዐለይሂሙ ሰለላም) ናቸው::

ســ١٧) اُذْكُرْ ثَلَاثَةً مِنْ أَسْمَاءِ الْمَلَائِكَةِ.

ጥ _17 :- ከመልዓክት ስሞች ውስጥ ሶስቱን ጥቀስ?

ج ـ ١٧) جِبْرِيْلُ، وَمِيْكَائِيْلُ، وَإِسْرَافِيْلُ.

መ_17 :- ጂብሪል፣ ሚካዔል፣ ኢስራፌል

س ـ ١٨) مَاهِيَ الْكُتُبُ السَّمَاوِيَّةُ الَّتِيْ أَنْزَلَهَا اللهُ ؟ وَعَلَىٰ مَن نَّزَلَتْ ؟

ጥ _18 :- አላህ ያወረዳቸው መለኮታዊ መጽሐፍቶች ምን ምንድናቸው? በእነማንስ ወረዱ?

ج ـ ١٨) ☜ صُحُفُ إِبْرَاهِيْمَ وَمُوْسَىٰ (عَلَىٰ إِبْرَاهِيْمَ وَمُوْسَىٰ،)

☜ الزَّبُوْرُ (عَلَىٰ دَاوُدَ،) ☜ التَّوْرَاةُ (عَلَىٰ مُوْسَىٰ،) ☜ الْإِنْجِيْلُ (عَلَىٰ عِيْسَىٰ،)

☜ الْقُرْآنُ الْكَرِيْمُ (عَلَىٰ مُحَمَّدٍ عَلَيْهِ الصَّلَاةُ وَالسَّلَامُ.)

መ_18 :- ❶☞ ሱሁፍ (በነቢዩላህ ኢብራሂም እና በነቢዩላህ ሙሳ ዐለይሂማስሰላም)

❷☞ ዘቡር (በነቢዩላህ በዳውድ ዐለይሂስሰላም)

❸☞ ተውራት (በነቢዩላህ ሙሳ ዐለይሂስሰላም)

❹☞ ኢንጂል (በነቢዩላህ ዒሳ ዐለይሂስሰላም)

❺☞ ቁርኣን (በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ) የወረዱ ናቸው።

س ـ ١٩) مَتَىٰ تَقُوْمُ السَّاعَةُ؟

ጥ _19 :- ቂያማህ (ትንሳዔ) የምትቆመው መቸናት?

ج ١٩) لَايَعْلَمُهَا إِلَّااللهُ.

መ_19 :- ከአላህ በስተቀር ማንም አያውቃትም።

س٢٠) مَا هِيَ دَارُ الْكَرَامَةِ؟

ጥ _20 :- የክብሯዋ ሀገር ማን ናት?

ج ٢٠) الْجَنَّةُ. መ_20 :- ጀነት ናት።

س٢١) كَمْ عَدَدُ أَبْوَابِ الْجَنَّةِ؟

ጥ _21 :- የጀነት በሮች ስንት ናቸው?

ج ٢١) ثَمَانِيَةٌ. መ_21 :- ስምንት ናቸው።

س٢٢) مَا هِيَ دَارُ الْعَذَابِ وَالْمَهَانَةِ؟

ጥ _22 :- የውርደትና የቅጣት ሀገር ማንናት?

ج ٢٢) النَّارُ (جَهَنَّمُ). መ_22 :- ኢሳት/ጀሀነም ናት።

س٢٣) كَمْ عَدَدُ أَبْوَابِ النَّارِ؟

ጥ _23 :- የጀሀነም በሮች ስንት ናቸው?

ج ٢٣) سَبْعَةٌ. መ_23 :- ሰባት ናቸው።

ጥ _24 :- ጠላትህ ማንነው? س٢٤) مَنْ عَدُوُّكَ؟

ج ـ ٢٤) عَدُوِّيْ هُوَ الشَّيْطَانُ الرَّجِيْمُ.

መ_24 :- ጠላቴ ከአላህ እዝነት የራቀው ፣እርጉም የሆነው ሰይጣን ነው።።

ጥ _25 :- ነቢይህ ማን ናቸው?

س ـ ٢٥) مَنْ نَّبِيُّكَ؟

ج ـ ٢٥) مُحَمَّدٌ ﷺ.

መ_25 :- ነቢዩ ሙሐመድ(ﷺ) ናቸው።።

س ـ ٢٦) مَا اسْمُ أَبِيْهِ وَأُمِّهِ؟

ጥ _26 :- የአባት፤ እናታቸው ስም ማንነው?

ج ـ ٢٦) أَبُوْهُ عَبْدُ اللهِ، وَأُمُّهُ آمِنَةُ.

መ_26 :- አባታቸው ዐብደላህ እናታቸው አሚነህ ናት።።

س ـ ٢٧) مَتَىٰ وُلِدَ النَّبِيُّ صَلَّىٰ اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ؟ وَفِي أَيِّ بَلَدٍ؟

ጥ _27 :- ነቢዩ(ﷺ) መች እና የት ሀገር ተወለዱ?

ج ـ ٢٧) فِيْ عَامِ الْفِيْلِ بِمَكَّةَ.

መ_27 :- በመካ ውስጥ“በዓመል ፊል”/በዝሆኑ ዓመት/ ነበር።።

س ـ ٢٨) إِلَىٰ أَيْنَ هَاجَرَ النَّبِيُّ صَلَّىٰ اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ؟

ጥ _28 :- ነቢዩ (ﷺ) ወደ የት ሀገርነው የተሰደዱት?

መ_28 :- ወደ መዲና ነው የተሰደዱት። جـ ٢٨) إِلَى الْمَدِينَةِ.

ሰ٢٩) أَيْنَ مَاتَ رَسُولُ اللهِ صَلَّىٰ اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ؟ وَأَيْنَ دُفِنَ؟

ጥ_29 :- ነቢዩ (ﷺ) የት ሞቱ? የትስ ተቀበሩ?

جـ ٢٩) مَاتَ وَدُفِنَ بِالْمَدِينَةِ.

መ_29 :- የሞቱትም የተቀበሩትም በመዲና ነው።

ሰ٣٠) مَنْ هُنَّ أُمَّهَاتُ الْمُؤْمِنِيْنَ ؟

ጥ_30 :- የምዕመናን እናቶች እነማንናቸው?

جـ ٣٠) زَوْجَاتُ النَّبِيِّ صَلَّىٰ اللهِ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ.

መ_30 :- የምዕመናን እናቶች የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ባለቤቶች ናቸው።

ሰ٣١) مَنْ هُمْ الْخُلَفَاءُ الرَّاشِدُوْنَ؟

ጥ_31 :- ቅን የሆኑ ምትኮች እነማን ናቸው?

جـ ٣١) ★ أَبُوْبَكْرٍ الصِّدِّيْقُ ★ عُمَرُ بْنُ الْخَطَّابِ ★عُثْمَانُ بْنُ عَفَّانٍ ★عَلِيُّ بْنُ أَبِي طَالِبٍ– رضي الله عنهم أَجْمَعِينَ.

መ_31 : - ★አቡበክር አስ-ሲዲቅ ★ዑመር ቢን አልኸጧብ ★ዑስማን ቢን ዐፋን ★ዐሊይ ቢን አቢጧሊብ ናቸው።

أسئلة وأجوبة في الفقه

س١) مَا هِيَ الصَّلَاةُ ؟

ጥ _1 :- ሶላት ምንድን ናት?

ج ١) الصَّلَاةُ هِيَ أَحَدُ أَرْكَانِ الْإِسْلَامِ، فَمَنْ تَرَكَهَا فَقَدْ كَفَر.

መ_1 : - ሶላት ከኢስልምና መሠረቶች ውስጥ አንዷናት፤ እሷን የተዋት በእርግጥም በጌታው ክዷል።

س٢) كَمْ صَلَاةً تَجِبُ عَلَىٰ الْمُسْلِمِ فِي الْيَوْمِ وَاللَّيْلَةِ؟

ጥ _2 :- በቀንና ሌሊት በአንድ ሙስሊም ላይ የስንት ግዜያት ሶላቶች ግዴታ ይሆኑበታል?

ج ٢) خَمْسُ صَلَوَاتٍ وَهِيَ:– الصُّبْحُ، وَالظُّهْرُ، وَالْعَصْرُ، وَالْمَغْرِبُ، وَالْعِشَاءُ.

መ_2 : - የአምስት ግዜያት ሶላቶች ናቸው።

እነሱም፡- ሱብሒ (ፈጅር ሶላት)፣ ዙሁር፣ ዐስር፣ መግሪብ እና ዒሻእ ናቸው።

س٣) كَمْ عَدَدُ رَكْعَاتِ كُلِّ صَلَاةٍ؟

ጥ _3 :- የእያንዳንዱ ሶላት ረከዓዎች ስንት ናቸው?

ጂ ፫) ☆ صَلَاةُ الصُّبْحِ (الْفَجْرِ) : رَكْعَتَانِ

☆ صَلَاةُ الظُّهْرِ : أَرْبَعُ رَكَعَاتٍ

☆ صَلَاةُ الْعَصْرِ : أَرْبَعُ رَكَعَاتٍ

☆ صَلَاةُ الْمَغْرِبِ : ثَلَاثُ رَكَعَاتٍ

☆ صَلَاةُ العِشَاءِ : أَرْبَعُ رَكَعَاتٍ

መ_3 : - ✪ሶላት አስ-ሱብህ (ፈጅር) ሁለት ረከዓ

✪ሶላት አዝዙህር አራት ረከዓ

✪ሶላተል ዐስር አራት ረከዓ ✪ሶላተል መግሪብ ሶስት ረከዓ
✪ሶላተል ዒሻእ አራት ረከዓ ናቸው።።

ሠ፬) مَاذَا يَجِبُ قَبْلَ الصَّلَاةِ؟

ጥ _4 :- ከሶላት በፊት ግዴታ የሚሆነው ምንድን ነው?

ጂ ፬) إِزَالَةُ النَّجَاسَةِ عَنِ الْبَدَنِ، وَالْمَلَابِسِ، وَمَكَانِ الصَّلَاةِ،

وَالْوُضُوءُ،

መ_4 :- ነጃሳን ከሰውነት፣ ከአልባሳት ፣ከመስገጃ ቦታ ማፅዳት እና ዉዱእ ማድረግ ናቸው።።

ጥ_5 :- እንዴት ዉዱእን ታደርጋለህ? ؟كَيْفَ تَتَوَضَّأُ (ሠ

ج ـ ٥) ⊂ أَنْوِيْ الْوُضُوْءَ بِقَلْبِيْ ثُمَّ أَقُوْلُ "بِسْمِ اللهِ"

⊂ ثُمَّ أَغْسِلُ كَفِّيْ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ

⊂ ثُمَّ أَتَمَضْمَضُ وَأَسْتَنْشِقُ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ

⊂ ثُمَّ أَغْسِلُ وَجْهِيْ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ

⊂ ثُمَّ أَغْسِلُ يَدَيَّ إِلَىٰ الْمِرْفَقَيْنِ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ

⊂ ثُمَّ أَمْسَحُ رَأْسِيْ مَعَ أُذُنَيَّ مَرَّةً وَاحِدَةً

⊂ أَغسِلُ رِجْلَيَّ إِلَىٰ الْكَعْبَيْنِ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ

መ_5 :- ➲ በመጀመሪያ በልቤ ዉዱእን በማሰብ ቢስሚላህ ኢላለሁኝ፤

➲ ከዚያም መዳፌን ሶስቴ አጥበዋለሁኝ፤

➲ከዚያም ሶስቴ እግሞጠሞጣለሁኝ፤ በአፍንጫዬም ሶስቴ ውሃን እየወሰድኩኝ አስወጣለሁኝ፤

➲ ከዚያም ፊቴን ሶስቴ አጥበዋለሁኝ፤

➲ ከዚያም እጆቼን ሶስቴ እስከ ክርኑ ድረስ አጥባቸዋለሁኝ

➲ ከዚያም ራሴን ከጆሮዬ ጋር አንዴ አብሰዋለሁኝ፤

➲ ከዚያም እግሮቼን እስከ ቁርጭምጭምቱ ድረስ ሶስቴ አጥባቸዋለሁኝ::

ሰ٦) مَا هِيَ نَوَاقِضُ الْوُضُوْءِ؟

ጥ _6 :- ውዱእን የሚፈቱ ነገራቶች ምንድን ናቸው?

ጂ ٦) الْخَارِجُ مِنَ السَّبِيْلَيْنِ، كَالْبَوْلِ، وَالْغَائِطِ ،وَالرِّيْحِ، وَغَيْرِهِ، وَأَكْلُ لَحْمِ الْإِبِلِ، وَالرِّدَّةُ عَنِ الْإِسْلَامِ، وَكَذَلِكَ النَّوْمُ،

መ_6 : - ከሁለቱ መፀዳጃ ሰውነቶቻችን የሚወጡ ነገሮች ፣እንደ ሽንት፣ ዓይነምድር፣ ፈስ የመሳሰሉ ነገራቶች፤ የግመል ስጋን መብላት፣ ከኢስልምና መቀልበስ፣ እንድሁም እንቅልፍ ናቸው::

ሰ٧) مَا السُّوْرَةُ الَّتِيْ تَجِبُ قِرَاءَتُهَا فِيْ الصَّلَاةِ؟

ጥ _7 :- በሶላት ውስጥ እንድትነበብ ግዴታ የሆነችዋ ምዕራፍ ምንድን ናት?

ጂ ٧) سُوْرَةُ الْفَاتِحَةِ.

መ_7 : - አል-ፋቲሃ ምዕራፍ ናት::

ሰ፦٨) مَاذَا يَقُوْلُ الْمُصَلِّيْ فِيْ الرُّكُوْعِ؟

ጥ _8 :- በሩኩዕ ውስጥ ሰጋጅ ምንይላል?

ጀ ٨) "سُبْحَانَ رَبِّيَ الْعَظِيْمِ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ."

መ_8 : - «ሱብሃነ ረቢየል ዐዚሚ» ሶስት ጊዜ (ለሀያሉ ጌታዬ ጥራት ተገባው) **ይላል።።**

ሰ፦٩) مَاذَا يَقُوْلُ الْمُصَلِّيْ فِي السُّجُوْدِ؟

ጥ _9 :- በሱጁድ ውስጥ ሰጋጅ ምን ይላል?

ጀ ٩) "سُبْحَانَ رَبِّيَ الْأَعْلَىٰ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ."

መ_9 : - «ሱብሃነ ረቢየል አዕላ» ሶስት ጊዜ (ከፍ ላለው ጌታዬ ጥራት ተገባው) **ይላል።።**

ሰ፦ مَاذَا يَقُوْلُ الْمُصَلِّيْ بَيْنَ السَّجْدَتَيْنِ؟

ጥ _10 :- ሰጋጅ በሁለት ሱጁዶች መካከል ምን ይላል?

መ_10 : - «ረብቢግፊርሊ» ጀ ١٠) "رَبِّ اغْفِرْلِيْ"

ሰ፦١١) مَاذَا يَقُوْلُ الْمُصَلِّيْ حِيْنَ يَرْفَعُ مِنَ الرُّكُوْعِ؟

ጥ _11 :- ሰጋጅ ከሩኩዕ በሚነሳበት ወቅት ምን ይላል?

ጀ ١١) الْإِمَامُ وَالْمُفْرِدُ يَقُوْلَانِ "سَمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدْ"

وَالْمَأْمُوْمُ يَقُوْلُ "رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدْ"

መ_11 : - ኢማምና፤ ቢቻውን የሚሰግድ ⇨«ሰሚዐሏሁ ሊመን ሀሚደህ፤ ረብበና ወለከል ሀምድ » (አሏህ የአመስጋኙን ምሥጋና ሰማ፤ ጌታችን ሆይ! ምስጋና ላንተ የተገባ ነው) ይላል።

⇨ተከታይ (መእሙም) የሆና፤ ሰው «ረብበና ወለከል ሀምድ» (ጌታችን ሆይ! ምስጋና ላንተ የተገባነው) ይላል።

ሠ١٢) اِقْرَإِ التَّشَهُّدَ وَالصَّلَاةَ عَلَىٰ النَّبِيِّ صَلَّىٰ اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَامِلًا.

ጥ_12 :- ተሸሁድንና ሶላት አለንነቢይን አሚልተ አንብብ?

ج ١٢) التَّحِيَّاتُ لِلّٰهِ وَالصَّلَوَاتُ وَالطَّيِّبَاتُ السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ وَرَحْمَةُ اللهِ وَبَرَكَاتُهُ السَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَىٰ عِبَادِ اللهِ الصَّالِحِينَ أَشْهَدُ أَن لَّا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُوْلُهُ.

اللّٰهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِ مُحَمَّدٍ كَمَا صَلَّيْتَ عَلَىٰ إبراهيمَ وَعَلَىٰ آلِ إِبْرَاهِيْمَ إِنَّكَ حَمِيْدٌ مَّجِيْدٌ وَبَارِكْ عَلَىٰ مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِ مُحَمَّدٍ كَمَا بَارَكْتَ عَلَىٰ إِبْرَاهِيْمَ وَعَلَىٰ آلِ إِبْرَاهِيْمَ إِنَّكَ حَمِيْدٌ مَجِيْدٌ.

اللّٰهُمَّ إِنِّيْ أَعُوْذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ، وَمِنْ عَذَابِ جَهَنَّمَ، وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَحْيَا وَالْمَمَاتِ، وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَسِيْحِ الدَّجَّالِ.

መ_12 : - አትተሒይያቱ ሊልላሂ ወስሶለዋቱ ወጥጠይዪባቱ አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሀን ነቢይዩ ወረሕመቱልሏሂ ወበረካቱሁ አስሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲልላሂስ-ሷሊሂነ አሽሀዱ አንላ ኢላህ ኢልለልሏህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉልሏህ ::

አልሏሁምመ ሶልሊ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐመዲን ከማ ሶልለይተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ::

ወባሪክ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐመዲን ከማ ባረክተ

ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ ::

አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢል ቀብር፣ ወሚን ዐዛቢ ጀሀንነመ፣ ወሚን ፊትነቲል መህያ ወልመማቲ፣ ወሚን ፊትነቲል መሲሂድደጃል::

سـ١٣) كَيْفَ تُصَلِّيْ؟ صِفْهُ عَمَلِيًّا؟

ጥ _13 :- ሶላትን እነዴት ትሰግዳለህ? በተግባርም አሳይ?

جـ ١٣)... يَنْبَغِيْ أَنْ يُطَبِّقَ كُلُّ التَّلَامِيْذِ صِفَةَ الصَّلَاةِ عَمَلِيًّا.

መ_13 : - ... ሁሉም ተማሪ የሶላትን አፈፃፀም በሚገባ በተግባር ልያፀና ይገባል::

ســ١٤) مَاذَا يُبْطِلُ الصَّلَاةَ؟

ጥ _14 :- ሶላትን ምን ያበላሻታል?

جـ ١٤) الْأَكْلُ وَالشُّرْبُ، وَالْكَلَامُ عَمْداً، وَالضِّحْكُ، وَانْتِقَاضُ الْوُضُوءِ، وَالْحَرَكَةُ الْكَثِيرَةُ.

መ_14 : - መብላት፣ መጠጣት፣ሆን ብሎ መናገር፣መሳቅ፣ ውዱእን መፍታት እና የበዛ እንቅስቃሴን ማድረግ።

ســ١٥) مَا هِيَ تَحِيَّةُ الْإِسْلَامِ؟

ጥ _15 :- ኢስላማዊ ሰላምታ ምንድንናት?

جـ ١٥) اَلسَّلَامُ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَةُ اللهِ وبَرَكَاتُهُ.

መ_15 : - «አስሰላሙ ዐለይኩም ወረህመቱሏሂ

ወበረካቱህ» (ሰላም በእናንተ ላይ ፤ የአላህ እዝነቱና ረድዔቱም...)

ســ١٦) بِأَيِّ يَدٍ يَأْكُلُ الْمُسْلِمُ وَيَشْرَبُ؟

ጥ _16 :- ሙስሊም የሚበላው፤ የሚጠጣው በየትኛው እጁ ነው ?

جـ ١٦) بِالْيَدِ الْيُمْنَىٰ.

መ_16 : - በቀኝ እጁ ነው።

ሠ١٧) مَتَىٰ تَقُوْلُ :- "بِسْمِ اللهِ"

ጥ _17 :- «ቢስሚላህ» መች ትላለህ?

ጀ ١٧) ☜قَبْلَ الْأَكْلِ وَالشُّرْبِ ☜ وَقَبْلَ دُخُوْلِ الْخَلَاءِ

☜وَقَبْلَ دُخُولِ الْمَسْجِدِ وَبَعْدَ الْخُرُوجِ مِنْهُ ☜وَقَبْلَ خَلْعِ الْمَلَابِسِ.

መ _17 : - ☑ ከመብለትና ከመጠጣት በፊት ፤

☑ መፀዳጃ ከመግባት በፊት፤

☑ መስጂድ ከመግባት በፊትና ከእሱም ከተወጣ በኋላ ፤

☑ ልብስን ከማውለቅ በፊት ::

ሠ١٨) مَتَىٰ تَقُوْلُ :- "الْحَمْدُ لِلَّهِ".

ጥ _18 :- «አልሀምዱሊልላህ» መችትላለህ?

ጀ ١٨) بَعْدَ الْأَكْلِ وَالشُّرْبِ، وَعِنْدَالعُطَاسِ، وَبَعْدَ كُلِّ نِعْمَةٍ،

መ _18 : - ከምግብና ከመጠጥ በኋላ፣ በሚያስነጥሰን ግዜ፣ ከማንኛውም ፀጋ በኋላ

ሠ١٩) أَيُّ الْأَمَاكِنِ أَحَبُّ إِلَىٰ اللهِ تَعَالَىٰ؟

ጥ _19 :- አላህ ዘንድ እጅግ በጣም ተወዳጅ የሆኑ ቦታዎች የትናቸው?

ጀ ١٩) الْمَسَاجِدُ.

መ_19 : - መስጂዶች (መስገጃ ስፍራዎች) ናቸው።።

ሰ٢٠) مَا هُوَأَفْضَلُ أَيَّامِ الْأُسْبُوْعِ؟

ጥ _20 :- ከሳምንቱ ቀናቶች በላጭ የሆነው ቀን ማንነው?

ጀ ٢٠) يَوْمُ الجُمُعَةِ.

መ_20 : - የጁሙዓ ቀን ነው።።

ሰ٢١) مَا هِيَ أَفْضَلُ لَيْلَةٍ فِي السَّنَةِ؟

ጥ _21 :- ከዓመቱ ሌሊቶች በላጭ የሆነችዋ ሌሊት ማንናት?

ጀ ٢١) لَيْلَةُ الْقَدْرِ.

መ_21 : - «ለይለቱል ቀድር» የውሳኔዋ ሌሊት ናት።።

ሰ٢٢) مَا هُوَأَفْضَلُ الشُّهُوْرِ؟

ጥ _22 :- ከወራቶች በላጭ የሆነው ወር ምንድን ነው?

መ_22 : - የረመዳን ወር ነው።። ጀ ٢٢) شَهْرُ رَمَضَانَ.

ሰ٢٣) مَا هِيَ أَعْيَادُ الْإِسْلَامِ؟

ጥ _23 :- የኢስላም በዓላቶች ምን ምንድን ናቸው?

ጀ ٢٣) عِيْدُ الْأَضْحَىٰ وَعِيْدُ الْفِطْرِ.

መ_23 : - ዒዱል አድሃ እና ዒዱል ፊጥር ናቸው።።

ሰ٢٤) مَتَىٰ نَسْتَعِيْذُ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيْمِ؟

ጥ_24 :- እርጉም እና ከአላህ እዝነት የተባረረ ከሆነው "ሰይጣን በአላህ መችነው የምንጠበቀው?

جـ ٢٤) ●قَبْلَ قِرَاءَةِ الْقُرْآنِ ●عِنْدَ الْوَسْوَسَةِ

●قَبْلَ دُخُوْلِ الْخَلَاءِ ●عِندَ سَمَاعِ نَهِيقِ الْحِمَارِ ●عِنْدَالْغَضَبِ.

መ_24 : - ⇨ ቁርኣንን ማንበብ ከመጀመራችን በፊት፣

⇨ ሸይጣን በሚጎተጎትበት ግዜ፣

⇨ መፀዳጃ ከመግባታችን በፊት፣

⇨ የአህያ ድምፅ በምንሰማበት ግዜ፣

⇨ በቁጣ ግዜ ናቸው።።

أسئلة وأجوبة في السيرة

س١) مَنْ سَيِّدُنَا مُحَمَّدٌ ﷺ؟

ጥ _1 :- አለቃችን ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ማንናቸው?

ج ١) هُوَ رَسُوْلُ اللّٰهِ إِلَىٰ النَّاسِ أَجْمَعِيْنَ.

መ_1 : - ወደ ሰው ዘር በአጠቃላይ የተላኩ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው::

س٢) مَا نَسَبُهُ ﷺ؟

ጥ _2 :- የዘር ሀረጋቸው እንዴት ነው?

ج ٢) هُوَ: مُحَمَّدُ بِنْ عَبْدِ اللهِ بِنْ عَبْدِ الْمُطَّلِبِ بِنْ هَاشِمِ...

وَهُوَ: قُرَشِيٌّ عَرَبِيٌّ وَأُمُّهُ: آمِنَةُ بِنْتُ وَهَبٍ بِنْ عَبْدِ مَنَافٍ.

መ_2 : - ሙሐመድ ቢን ዐብደላህ ቢን ዐብዱል ሙጥጠሊብ ቢን ሃሺም ..... እሳቸው ጎሳቸው ቁረሺይ ሲሆን ዐረባዊ ናቸው::
፤እናታቸው አሚነቱ ቢንቱ ወሀብ ቢን ዐብዱ መናፍ ....

س٣) أَيْنَ وُلِدَ ﷺ؟

ጥ _3 :- ነቢዩ (ﷺ) የት ተወለዱ ?

ج ـ ٣) وُلِدَ بِمَكَّةَ الْمُكَرَّمَةِ.

መ_3 : - በተከበረችዋ መካ ላይ ተወለዱ::

ሰ ـ ٤) مَتَىٰ وُلِدَ النَّبِيُّ ﷺ ؟

ጥ _4 :- ነቢዩ (ﷺ) መች ተወለዱ?

ج ـ ٤) وُلِدَ ﷺ يَوْمَ الْإِثْنَيْنِ عَامَ الْفِيْلِ.

መ_4 : - ሰኞ ለት በዚሆኑ ዓመት ተወለዱ::

ሰ ـ ٥) هَلْ يُعْرَفُ الشَّهْرُ الَّذِيْ وُلِدَ فِيْهَا وَعَدَدُ أَيَّامِهَا؟

ጥ _5 :- ነቢዩ (ﷺ) የተወለዱበት ወር እና የቀን ቁጥሩ ይታወቃልን?

ج ـ ٥) لَا يُعْرَفُ بِالضَّبْطِ الشَّهْرُ الَّذِيْ وُلِدَ فِيْهِ وَلَاعَدَدُ أَيَّامِهِ.

መ_5 : - የተወለዱበት ወርም ሆነ የቀን ቁጥር በተጨባጭ አይታወቅም::

ሰ ـ ٦) لِمَذَا لَا يُعْرَفُ بِالضَّبْطِ؟

ጥ _6 :- ለምን በተጨባጭ አይታወቅም?

ج ـ ٦) لِأَنَّهُ وُلِدَ فِيْ زَمَنٍ لَمْ يَكُنْ فِيْهِ تَسْجِيْلٌ لِلْمَوَالِيْدِ.

መ_6 : - ምክንያቱም ነቢዩ (ﷺ) የተወለዱት ልደት

በማይመዘገብበት ዘመን ነውና::

ሰ_ ٧) مَتَىٰ تُوُفِّيَ وَالِدُهُ ﷺ؟

ጥ _7 :- አባታቸው መች ሞተ?

ጅ ٧) مَاتَ أَبُوْهُ وَهُوَ فِيْ بَطْنِ أُمِّهِ.

መ_7 : - አባታቸው የሞተው እሳቸው በእናታቸው ማህፀን እያሉ ነበር::

ሰ_ ٨) مَنْ هِيَ اللَّوَاتِيْ أَرْضَعْنَهُ ؟

ጥ _8 :- የነቢዩ (ﷺ) አጥቢዎች እነ ማን ናቸው?

ጅ ٨) أُمُّهُ آمِنَةُ، وَثُوَيْبَةُ مَوْلَاةُ أَبِيْ لَهَبٍ، وَحَلِيْمَةُ السَّعْدِيَّةُ،

መ_8 : - እናታቸው አሚና፣ ሱይባ የአቡለሀብ አገልጋይ የነበረችዋ እና ሐሊመቱ አስ-ሰዕዲይየህ ናቸው::

ሰ_ ٩) كَمْ سَنَةً مَكَثَ عِنْدَ حَلِيْمَةُ السَّعْدِيَّةُ؟

ጥ _9 :- ሐሊመቱ አስ-ሰዕዲይየህ ዘንድ ስንት ዓመታትን ተቀመጡ?

ጅ ٩) أَرْبَعَ سَنَوَاتٍ.

መ_9 : - አራት ዓመታትን ::

ሰ_ ١٠) مَتَىٰ تُوُفِّيَتْ أُمُّهُ ﷺ؟

ጥ _10 :- እናታቸው መች ሞቱች?

ج ١٠) تُوُفِّيَتْ أُمُّهُ وَعُمْرُهُ سِتُّ سَنَوَاتٍ.

መ_10 : - የነቢዩ (ﷺ) እናት የሞተችው ዕድሜያቸው ስድስት ዓመት ሲሞላቸው ነበር።

س١١) مَنْ هِيَ حَاضَنَتْهُ بَعْدَ وَفَاتِ أُمِّهِ؟

ጥ _11 :- ከእናታቸው ሞት በኋላ ሞግዚት ማን ሆነችላቸው?

ج ١١) أُمُّ أَيْمَنْ مَوْلَاتُ أَبِيْهِ.

መ_11 : - የአባታቸው አገልጋይ የነበረችዋ ኡሙ አይመን ናት።

س١٢) مَنْ قَامَ بِتَرْبِيَتِهِ بَعْدَ وَفَاتِ أُمِّهِ؟

ጥ _12 :- ከእናታቸው ሞት በኋላ እሳቸውን የማሳደግ ሀላፍትና ላይ ማን ቆመ?

ج ١٢) جَدُّهُ عَبْدُ الْمُطَّلِبُ.

መ_12 : - አያታቸው ዐብዱል ሙጥጠሊብ።

س١٣) كَيْفَ كَانَ حَالُهُ مَعَ جَدِّهِ؟

ጥ _13 :- የነቢዩ(ﷺ) ሁኔታ ከአያታቸው ጋር እንዴት ነበር?

ج ـ ١٣) كَانَ جَدُّهُ يُحِبُّهُ أَكْثَرَ مِنْ أَوْلَادِهِ، وَيُجْلِسُهُ عَلَىٰ فِرَاشِهِ،

መ_13 : - አያታቸው በእጅጉኑ የሚወዳቸው፤ በእርሱ ፍራሽም ያሚያስቀምጣቸው ነበር::

س ـ ١٤) مَتَىٰ تُوُفِّيَ جَدُّهُ؟

ጥ _14 :- አያታቸው መች ሞተ?

ج ـ ١٤) تُوُفِّيَ جَدُّهُ وَعُمْرُهُ ثَمَانِيْ سَنَوَاتٍ.

መ_14 : - ዕድሚያቸው ስምንት ዓመት ሲሞላቸው አያታቸው ሞተ::

س ـ ١٥) مَنْ كَفَلَهُ بَعْدَ وَفَاتِ جَدِّهِ؟

ጥ _15 :- አያታቸው ከሞተ በኋላ ማን ሀላፍትናቸውን ወሰደ?

ج ـ ١٥) كَفَلَهُ عَمُّهُ أَبُوْ طَالِبٍ.

መ_15 : - አጎታቸው አቡጧሊብ ሀላፊ ሆናቸው::

س ـ ١٦) بِمَاذَا كَانَ يَشْتَغِلُ فِيْ صِغَرِهِ؟

ጥ _16 :- በልጅንነታቸው በምን ስራ ይሰማሩ ነበር?

ج ـ ١٦) كَانَ يَرْعَىٰ الْغَنَمَ لِأَهْلِ الْمَكَّةَ.

መ_16 : - ለመካ ሰዎች በግ እና ፍየልን ያግዱ ነበር::

ســ١٧) مَتَىٰ سَافَرَ إِلَىٰ الشَّامِ لِأَوَّلِ مَرَّةٍ؟

ጥ _17 :- ለመጀመሪያ ግዜ ወደ ሻም መች ተጓዙ?

جـ ١٧) مَعَ عَمِّهِ فِيْ السَّنَةِ الثَانِيَةَ عَشَرَ مِنْ عُمُرِهِ.

መ_17 : - ከአጎታቸው ጋር በ12 ዓመታቸው ላይ ነበር።

ســ١٨) مَتَىٰ تَزَوَّجَ بِخَدِيْجَةَ؟

ጥ _18 :- ኸዲጃን ያገቧት መች ነበር?

جـ ١٨) عِنْدَمَا بَلَغَ الْخَامِسَةَ وَالْعِشْرِيْنَ مِنْ عُمُرِهِ.

መ_18 : - ዕድሜያቸው 25 ዓመት ሲሞላቸው ነበር።

ســ١٩) كَمْ سَنَةً أَقَامَ مَعَهَا؟

ጥ _19 :- ስንት ዓመትን ከእርሷ ጋር ቆዩ?

جـ ١٩) أَقَامَ مَعَهَا خَمْسًا وَعِشْرِيْنَ سَنَةً.

መ_19 : - 25 ዓመታትን ከእርሷ ጋር ቆይተዋል።

ســ٢٠) مَتَىٰ جَدَّدَتْ قُرَيْشٌ بِنَاءَ الْكَعْبَةِ؟

ጥ _20 :- ቁረይሾች የከዕባን ግንባታ መች ነበር ያደሱት?

جـ ٢٠) لَمَّا بَلَغَ خَمْسًا وَثَلَاثِيْنَ سَنَةً.

መ_20 : - ነቢዩ (ﷺ) ዕድሜያቸው 35 ዓመት ሲሞላቸው ነበር::

ሰ٢١) هَلْ اشْتَرَكَ مَعَ قُرَيْشٍ فِيْ بِنَائِهَا؟

ጥ _21 :- በከዕባ ግንባታ ከቁረይሾች ጋር ተሳትፎ አድርገዋልን?

ጀ ٢١) نَعَمْ، وَحَكَمَ بَيْنَهُمْ فِيْ وَضْعِ الْحَجَرِ الْأَسْوَدِ.

መ_21 : - አዎን፤ ሀጀረል አስወድን (ጥቁሩን ድንጋይ) በቦታው በማስቀመጥ ላይም በመሀከላቸው ፈራጅ ሁነዋል::

ሰ٢٢) بِمَاذَا اشْتُهِرَ بَيْنَ قَوْمِهِ؟

ጥ _22 :- ወገኖቻቸው ዘንድ በምን ይታወቁ ነበር?

ጀ ٢٢) بِجَمِيْعِ الْخِصَالِ الْمَحْمُوْدَةِ: كَالصِّدْقِ، وَالْأَمَانَةِ،وَالْحِلْمِ،...

መ_22 : - ምስጉን በሆኑ በህሪያቶች ሁሉ እንደ እውነተኝነት፣ ታመኝነት እና ቻይነት....

ሰ٢٣) بِمَاذَا لُقِّبَ بَيْنَ قَوْمِهِ؟

ጥ _23 :- ወገኖቻቸው ዘንድ በምን ቅፅል ይጠሩ ነበር?

ጀ ٢٣) بِالصَّادِقِ الْأَمِيْنِ.

መ_23 : - እውነተኛውና ታማኙ::

ســ ٢٤) مَتَىٰ أَحَبَّ الْإِبْتِعَادَ عَنِ النَّاسِ؟

ጥ _24 :- ከሰዎች መራቅን (ገለልተኝነትን) የመረጡት መች ነበር?

جـ ٢٤) حِيْنَمَا قَارَبَ الْأَرْبَعِيْنَ مِنْ عُمُرِهِ.

መ_24 : - ከእድሜያቸው 40ኛውን ሲቃረቡ ነበር።

ســ ٢٥) أَيْنَ كَانَ يَتَعَبَّدُ؟

ጥ _25 :- የትነበር አምልኳቸውን ይፈፅሙ የነበረው?

جـ ٢٥) فِيْ غَارِ حِرَاءَ.

መ_25 : - ሂራእ በተባለው ዋሻ ነበር።

ســ ٢٦) عَلَىٰ أَيِّ دِيْنٍ يَتَعَبَّدُ؟

ጥ _26 :- አምልኳቸውን ይፈፅሙ የነበሩት በየትኛው እምነት ሁነው ነበር?

جـ ٢٦) عَلَىٰ دِيْنِ إِبْرَاهِيْمَ عليه السلام.

መ_26 : - በነቢዩላህ ኢብራሂም ዐለይሂስሰላም እምነት ላይ ሁነው ነበር።

ســ ٢٧) مَتَىٰ بُعِثَ النَّبِيُّ ﷺ ؟

ጥ _27 :- ነቢዩ (ﷺ) መች ተላኩ?

ج ـ ٢٧) عَلَىٰ رَأْسِ أَرْبَعِيْنَ.

መ_27 : - በ40ኛው ዕድሜያቸው መጨረሻ ላይ።

س ـ ٢٨) كَيْفَ بَدَأَ الْوَحْيُ؟

ጥ _28 :- ወህዩ እንዴት ጀመረ?

ج ـ ٢٨) بَدَأَ الْوَحْيُ بِالرُّؤْيَةِ الصَّالِحَةِ.

መ_28 : - ወህዩ የጀመረው በጥሩ ህልም ነበር።

س ـ ٢٩) مَاذَا كَانَ حَالُ الْعَرَبِ قَبْلَ الْإِسْلَامِ؟

ጥ _29 :- የዐረቦች ሁኔታ ኢስልምና ከመምጣቱ በፊት እንዴት ነበር?

ج ـ ٢٩) كَانُوْا مُشْرِكِيْنَ، وَكَانُوْا يَقْتُلُوْنَ أَوْلَادَهُمْ خَوْفًا مِنَ الْجُوْعِ وَالْفَقْرِ، وَيَدْفِنُوْنَ بَنَاتَهُمْ وَهُنَّ أَحْيَاءٌ خَشْيَةَ الْعَارِ وَالْعَيْبِ.

መ_29 : - በአላህ አጋሪያን የነበሩ፣ ወንድ ልጆቻቸውን ረሓብንና ድህነትን በመፍራት የሚገድሉ ሴት ልጆቻቸውን ከነህይወታቸው በሰዎች መተቸትን ፈርተው ይቀብሯቸው ነበር።

ሠ ــ ٣٠) كَيْفَ بَدَأَ النَّبِيُّ ﷺ دَعْوَتَهُ؟

ጥ _30 :- ነቢዩ (ﷺ) ደዕዋቸውን (ጥሪያቸውን) እነዴት ጀመሩ?

ጀ ــ ٣٠) بَدَأَ دَعْوَتَهُ سِرًّا.

መ_30 : - ደዕዋቸውን (ጥሪያቸውን) የጀመሩት በምስጥር ነበር::

ሠ ــ ٣١) مَنْ أَوَّلُ مَنْ آمَنَ بِهِ مِنَ النِّسَاءِ؟

ጥ _31 :- ለመጀመሪያ ግዜ በነቢዩ (ﷺ) ከሴቶች ያመነችዋ ማን ናት?

ጀ ــ ٣١) خَدِيْجَةُ رضي الله عنها.

መ_31 : - ኸዲጃ رضي الله عنها ናት::

ሠ ــ ٣٢) مَنْ أَوَّلُ مَنْ آمَنَ بِهِ مِنَ الرِّجَالِ؟

ጥ _32 :- ለመጀመሪያ ግዜ በነቢዩ (ﷺ) ከወንዶች ያመነው ማን ነው?

ጀ ــ ٣٢) أَبُوْبَكْرٍ الصِّدِّيْقُ رضي الله عنه.

መ_32 : - አቡበክር አስ-ሲዲቅ رضي الله عنه ነው::

ሰ٣٣) مَنْ أَوَّلُ مَنْ آمَنَ بِهِ مِنَ الصِّبْيَانِ؟

ጥ _33 :- ለመጀመሪያ ግዜ በነቢዩ (ﷺ) ከልጆች ያመነው ማን ነው?

ጀ ٣٣) عَلِيُّ ابْنُ أَبِيْ طَالِبٍ ﷺ.

መ_34 : - ዐሊይ ኢብኑ አቢጧሊቢ ﷺ ነው።።

ሰ٣٤) مَنْ أَوَّلُ مَنْ آمَنَ بِهِ مِنَ الْمَوَالِيْ؟

ጥ _34 :- ለመጀመሪያ ግዜ በነቢዩ (ﷺ) ከአገልጋዮች ያመነው ማን ነው?

ጀ ٣٤) زَيْدُ بْنُ ثَابِتٍ ﷺ.

መ_34 : - ዘይድ ኢብኑ ሳቢት ﷺ ነው።።

ሰ٣٥) كَمْ سَنَةً إِسْتَمَرَّتْ الدَّعْوَةُ السِّرِّيَّةِ؟

ጥ _35 :- በምስጥር ይደረግ የነበረው ደዕዋ (ጥሪ) ለስንት ዓመታት ቀጠለ?

ጀ ٣٥) لِثَلَاثِ سَنَوَاتٍ ثُمَّ أُمِرَ بِالْجَهْرِ.

መ_35 : - ለሶስት ዓመታት ቀጠለ ከዚያም ነቢዩ (ﷺ) በይፋ እንዲጣሩ ታዘዙ።።